# ከሀዲና ባንዳ የድል እንቅፋቶች

ኢትዮጵያ ሀገራችን በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ሳትወድቅ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች ብቸኛ ሀገር ናት ሲባል ለተረት ተረት ሳይሆን ብዙ ትርጉም ያለው ነው። ቅኝ ገዢዎች ዓለምን ለመቀራመት፣ በተለይ አፍሪካንና ሌሎች ታዳጊ ሀገሮችን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የየሀገሮቹን የተፈጥሮ ሀብት ለመመዝበር፣ ሕዝቦችን ለባርነት ለመዳረግ ሲራወጡ ኢትዮጵያን ሳይፈልጓት ቀርተው ወይም እራሷ የወራሪዎች ተባባሪ ሆና አይደለም። በወቅቱ የነበሩትና ኢትዮጵያን በየጊዜው ያስተዳደሯት መሳፍንት ግዛታቸውን ከማስፋፋት ባሻገር ኢትዮጵያን በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት እንድትተዳደር ለማድረግ ከነበራቸው ጽኑ ፍላጎት አንፃር ኢትዮጵያዊነት ስሜት፣ ሀገር የመውደድ ስሜት አድሮባቸው ኢትዮጵያዊነትና ሀገር ወዳድነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ መለያ እንዲሆን አስተዋጽዎ በማድረጋቸው ለማንም ወራሪ ኃይል እንዳትበገር ሆናለች። ሀገራችን ነፃነቷን ጠብቃ ስትኖር ሁሌም ሀገሬ፣ ሁሌም ዳር ድንበሬ፣ ሁሌም ባንዲራዬ የሚል ስሜት በሁላችንም ደም ውስጥ ሰርፆ ገብቷል። የአባት የናቶቻችን ጀግንነት ብለን ስናወራ፣ ከአበው የወረስነው የጀግንነት ስሜት ብለን ስንናገር፣ አድዋን በያመቱ ስንዘክር ወዘተ. ታሪክ ሳይበረዝና ሳይጠፋ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ነው። ኢትዮጵያዊነት ፥ ጀግንነት፣ አትንኩኝ ባይነት፣ ኩሩነት፣ እንግዳ ተቀባይነት መሆኑን ትውልድ በተተካ ቁጥር ይበልጥ እየጠነከረ እንዲሄድ ከማድረግ የመነጨ መለያ ስሜታችን ነው።

ሀገራችን ነፃነቷን ጠብቃ፣ በማንም ወራሪ ኃይል ሳትደፈር፣ ብትደፈርም አይቀጡ ቅጣት ቀጥታና አሳፍራ የመለሰችበት ጉዞ ብዙ ውጣ ውረድ የነበርሩትና ከፍተኛም መስዋዕትነትን እየጠየቀና እየተከፈለበት የመጣ እንደነበር የሚካድ አይደለም። የሀገርን ሉዓላዊነትና ክብር የመጠበቅና ለትውልድ የማስተላለፍ ጉዞ በርካታ ሕይወትን የጠየቀና እየጠየቀ ያለ ጉዳይ ነው። በየጊዜው የተፈራረቁት የመሳፍንት አገዛዝ ከነበረው የጭቆናና የኋላ ቀርነት አስተዳደር ባሻገር በሀገር ጉዳይ ሁሉም ቀናዊ አመለካከትና ስሜት ነበራቸው ቢባል ሀቅ ነው። በሀገራችን ሁልጊዜም የውጭ ወራሪ በሚያንዣብብበት ወቅት የውስጥ ቅራኔዎች በሙሉ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ ብለው የሀገር ጉዳይ ይውለበለባል። ቀዳማይ ይሆናል። ሁሉም ጎራ በአንድነት ይነሳል። በአንድ ድምጽ ይጨሃል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በየጊዜው በውስጥም ሆነ በውጭ ጉዳዮችን ከጠላት ያላነሱ ሀገር በቀል ባንዳዎች፣ ከሃዲዎች ሁሌም ይነሳሉ። ይበቅላሉ። በጣሊያን የአምስት አመቱ የፍልሚያ ገዜ ከጠላት ጐራ ተሰልፈው ሀገርንና ሕዝብን የወጉ የታሪክ አተላዎች ቀላል አልነበሩም። ባንዳዎች። በወቅቱ የሀገርን ሚስጥርና ህልውና ለጠላት አሳልፈው በመስጠት ለሀገሪቷ ነፃነትና ሉዋላዊነት እየተናነቁ የነበሩትን አርበኞች በቅጡ ጎድተዋል። በአድራጎታቸውም ንብረት፣ ሕይወት፣ ሀገር አጥፍተዋል። የማይቀረው የነፃነትና የድል ቀን እንዲራዘም አስተዋጽዎ አበርክተዋል። ያ ሁሉ እሩጫቸው ለጊዜያዊ ጥቅም ከመሆኑም ባሻገር ሆን ብለው ሀገሪቷንና ሕዝቧን ከጥንት ጀምረው ሊጎዷት ትልቅ ዕልም ከአላቸው የውጭ ኃይሎች ጋር በሀገር ጉዳይ ላይ የመሞዳሞድና ሕልውናን የመሸጥ ጉዳይ እንደነበርም ልንዘነጋው አይገባንም። ይህንን አይቶና ታዝቦ በየጊዜው ብቅ ለሚሉ ሀገር በቀል ባንዳዎችና ከሃዲዎች፣ ሕዝብን እየከዱ ከወራሪ፣ ከሕዝብና ሀገር ጠላት ጐን ሰልፋቸውን ለሚያደርጉት እንዲህ ሲል የተቀኘላቸው፣

"ጠላትማ አንደኛውን ጠላት ነው፣ አስቀድሞ መምታት አሾክሻኪውን ነው።"

የታሪክ ድግምግሞሽ የተፈጥሮ ልገሳችን ይመስል ሀገርና ሕዝብን እየከዱ ወደ ጠላት ጐራ የሚሰለፉ ሀገር በቀል ባንዳዎች ከጥንት ጀምሮ ፥ በአድዋ ጦርነት፣ በአምስት ዓመቱ የጣሊያን ወረራ፣ በሶማሊያ ጦርነት ወቅት ወዘተ. አሁንም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም። በሀገር

ውስጥም ብዝበዛና ጭቆና፣ አፈናና ጭፍጨፋ በቃኝ ብሎ ሕዝብ ለነፃነቱ፣ ለመብቱ፣ ለክብሩ በየጊዜው በአለው አገዛዝ ላይ ሲያምጽና ሲነሳ የብሶቱ ተካፋይ፣ ወገኑ በመምሰል ውስጥ ውስጡን ለገዥው መደብ እየሠሩ ሚስጥሩንና እንቅስቃሴውን አሳልፈው እየሰጡበት የመከራ ገፈት ቀማሽ እንዲሆን ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል። የነፃነት ድሉ፣ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ዘመኑ እንዲራዘም በየጊዜው የሚሰነቀሩበት ባንዳዎችና ከሃዲዎች ከፍተኛ አስተዋጽዎ አድርገዋል። አሁንም እያደረጉ ይገኛሉ።

በአፄው አገዛዝ ዘመን ተሞክሮ የነበረው የ1953 ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍ በአካሄዱ ላይ ከነበረው ቸልተኝነት በተጨማሪ ውስጥ ውስጡን አብረው ያራገቡና በኋላም ድርጊቱን የከዱ ለመኖራቸው ታሪክ የዘገበው ሃቅ ነው። ከዚያም በየጊዜው የሚደረገውን የተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ ከተማሪውና ከህዝቡ ጎን የተሰለፉ በመምሰል ብርቅዬ ኢትዮጵያዊ ወጣት ተማሪዎችን ያሳፈኑ፣ ያስገደሉ ወዳጅ መሳይ ጠላቶች እያሌ ነበሩ።

በፋሽስታዊው ወታደራዊ አገዛዝ ዘመን በገሃድ ከደርግ ጎን ከተሰለፉት ባንዳ ምሁራን በተጨማሪ የሀገሪቷን የወደፊት አካሄድ አቅጣጫው ወደ መበታተን፣ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በአፍሪካ አህጉር ጉልታ እንዳትታይ በውጭ ጠላቶች ለተነደፈው ስትራተጂያዊ ስልት ድጋፍ በመስጠትና በመንቀሳቀስ ከፍተኛ ፀረ - ኢትዮጵያና ፀረ - ሕዝብ አስተዋጽዎ በማድረግ አሁን ለአለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ የራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል። ደርግ ከአለበት ስልጣኔን አትንኩ አባዜ ማንንም ተቀናቃኝ ያለምንም ማወላወል መግደል መመሪያው ነበር። የሕዝቡ ንቅናቄና አመጽ እየበረታና እየጠነከረ መምጣት፣ የደርግ ሕልውናና በስልጣን የመቆየት ያለመቆየት ጉዳይ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ፣ ደርግ የመጨረሻውን የመፈራገጥ ምት ያታ፣ ዕድሜ፣ ዘር፣ ሃይማኖት ሳይለይ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ላይ በማሳረፍና በሀገሪቷ ላይ ከፍተኛ ሸብር በማካሄዱ አንድ ትውልድ አጥፍቶ ለተወሰነ ዓመታት በስልጣን ለመቆየት ከአበቁት አንደኛው ምክንያት በራሱ በሕዝቡና በእንቅስቃሴው ውስጥ የበቀሉ ከሀዲ ባንዳዎች (አንጃዎች) አስተዋጽዎ የሚዘነጋ አይደለም።

ኢሕአፓ በ1966 ዓ.ም. የተነሳው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መሪ በማጣቱና በወታደራዊው ኃይል በመነጠቁ የሕዝቡን ትግል ለመምራት ኃላፊነቱን የወሰደና ከፍተኛ ፀረ - ፋሽስት ተጋድሎ ያደረገ ብቸኛ የሕዝብ ፓርቲ ነበር። በወቅቱ ለምን ይህ አልተደረገም የሚባሉትን እንተወውና ድርጅቱን ይበልጥ ሊጐዳውና ለፋሽስታዊው ደርግ አመታት ሊመቻች ከአስቻሉት አንዱና ዋነኛው ምክንያት በውስጡ የበቀሉት ሀገር፣ ሕዝብና ፓርቲ የከዱ ከሃዲ ባንዳዎች/አንጃዎች ነበሩ ቢባል ማጋነን ሳይሆን ሃቅን መናገር ነው። የነኝህ በውጭ ኃይሎች ጠንሳሽነትና በተቀነባበረ መንገድ ውስጥ ውስጡን የሕዝብ ወገን መስለው፣ ድርጅቱን ሰርስረው ገብተው፣ የድርጅቱን ሚስጥር ለጠላት አሳልፈው በመስጠት ኢትዮጵያ የማትተካቸውን ብርቅዬ ታጋዮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለፋሽስት ጥይት አስረክበዋል።

በ1983 ዓ.ም. በወታደራዊው አገዛዝ ላይ የተደረገውን የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በረቀቀ ዘዴና ተንኮል ከጥንሰሳው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሂደት የሀገሪቷ የውጭ ጠላቶችና የውስጥ ባንዳዎች በመተባበር ያደረጉት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በጊዜው የነበሩትን ወታደራዊ የጦር መኮንኖች በመፈንቅለ መንግሥት ስም አንቀሳቅሶ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ማስመታት ማለት በአንድ በኩል ወያኔና ሻቢያ እያደረጉ ላለው እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ሲኖረው በሌላ በኩል ሀገሪቷ ወደፊት ምንም ዓይነት የተጠናከረ ወታደራዊ ተቋም እንዳይኖራት ለታቀደው ስልት ቅድመ ዝግጅት ነበር።

የውጭ ተላቶች ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንዳትኖር ለምን ፈለጉ? እጅግ ብዙ ሊባል ይችላል። ሀገራችን በወራሪ ኃይል ሳትገዛ በመኖሯ በሕዝባችን ውስጥ የኩራት መንፈስ ከመፍጠሩም በላይ ኢትዮጵያዊነትና ሀገር ወዳድነትን መንፈስ አጠንክሮበታል። በወቅቱም በቅኝ ግዛትነት የተያዙ የአፍሪካ ሀገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ቀንበር መላቀቅ እንደሚችሉ አርሃያ በመሆን ትምህርት የሆነች ሀገር ሆና ለተገኘውም የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ መውጣት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አድርጋለች። ወደ መጨረሻ ላይ ተንኮለኞቹ ቢያስቀሙትም ማንኛውም ነፃ የሚወጡ የአፍሪካ ሀገሮች አረንጓዴ/ቢጫ/ቀይ ሰንደቃችንን በተለያየ አቀማመጥ በመጠቀም ሀገራችን የነፃነት ተምሳሌት እንድትሆን አድርጓታል።

ሀገራችን ነፃነቷን ጠብቃ መኖሯ ያልተበረዘ ቋንቋ፡ ባህል፡ ሃይማኖት፡ የራሷ የሆነ ፊደል እንዲኖራት አድርጓል። የተባበሩት መንግሥታት መስራች፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መስራች፡ የመጀመሪያዋ የዓለም ሰብዓዊ መብት ሰነድ ፈራሚ አፍሪካዊት ሀገር እየሆነች ጎልታ መምጣት ዳግም አፍሪካን ለመቀራመት እያሰቡ ላለው ዓላማቸው በዚህ አካሄድ ከቀጠለች አስጊ እንደምትሆንባቸው የገመቱት ከዛሬ ስንትና ስንት ዓመት በፊት ነበር። ኢትዮጵያ፡ ሀገሬን፡ ሕዝቤን በሚል፡ ለማንም የባዕድ ኃይል በማያጐበድድ የሕዝብ መንግሥት ከተዳደረች፡ የሕዝቡን መብት የሚያዳምጥ፡ ሕዝብ በሀገሩና በህልውናው ወሳኝ ሚና የሚጫወትበት መንግሥት ከተመሰረተ የነገ ተልዕኮአቸው ሙሉ በሙሉ ተሰናከለ ማለት ነው። የራሷን የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ መጠቀም ትጀምራለች። ረሃብ፡ ድህነት፡ በሽታ፡ ጦርነት ከሀገሪቷ ተንኮታኩተው በነበር ይቀራሉ። ይህ አርሃያ ደግሞ ለሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች መባነን ያስከትላል። በመሆኑም ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን አፍሪካ የባዕዳን ጥገኛ ላትሆን፡ አፍሪካ አልገዛም ልትል ቀዳዳ መክፈት ስለሚሆን በእንጭጩ መቀጨት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ያሰቡበት ጥንት ነው።

ለጊዜው ጋብ ያለ ቢመስልም የአረቡ ዓለም ኢትዮጵያን የሚያይበት የራሱ የሆነ አካሄድ ቀላል አልነበረም። ለወያኔና ሻቢያ ዋና መጠናከር "አረባዊ ነን" እስከማለት መድረሳቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ዓባይንና ወንዞቿን በአግባቡ የመጠቀም ጉዳይ የሚመጣው ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ሲሆን ነው። ይህንንና መሰል የተፈጥሮ ሀብቷን እንድትጠቀም ደግሞ ወሳኞቹ፡ ከልካዮቹና ፈቃጆቹ ባዕዳን ናቸው። ለዚህም ቀላሉ መንገዳቸው ኢትዮጵያ በሀገርነት እንዳትኖር ማድረጉ ብትኖርም እራሱን ለባዕድ ባስገዛ፡ የሀገር ደላላ፡ የሕዝብ ፀር፡ ሀገር በቀል ከሀዲዎችና ባንዳዎች መጠቀሙ ከሁሉም በላይ አመርቂ ሆኖ አግኝተውታል።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ በመንግሥት እየተዳደረች ያለችበት ወቅት አይደለም። ኢትዮጵያን አምባገነን፡ ወንበዴ፡ አሸባሪ፡ ገዳይ፡ ሀገር በቀል ወራሪ ቡድን ለጌቶቹ በቅኝ ይዟታል። ይህ ሀገር በቀል ወራሪ የባዕዳንን የወረራ ተግባር እየፈጸመ ይገኛል። ቢቻል የሀገሪቷ መንግሥት ነኝ በሚል ማደናገሪያው ውስጥ ውስጡን በረቀቀ ዘዴ የወደፊት ዕቅዳቸውን ማሳካት፥ ሀገሪቷን የማጥፋት፡ የመበታተን፡ በቁም የመግደል ተግባር ማከናወን። ይህ ደግሞ ለአለፉት 16 ዓመታት ተካሂዷል። አሁንም እየተካሄደ ይገኛል። በአፄው አገዛዝ ላይ የአመጸው ሕዝብ ለመብቱ፡ ለነፃነቱ፡ ከጭቆና ቀንበር ለመላቀቅ ያደረገው ነበር። ከፋሽስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ ጋር የተደረገው ፍልሚያ ለፍትህ፡ ለዲሞክራሲ፡ ለሕዝብ መንግሥት የተደረገ ፀረ - ፋሽዝም ተጋድሎ ነበር። ከወያኔ ጋር የሚደረገው ትግል ግን እነኝህን አካቶ የሀገርና የሕዝብን ህልውና ይጨምራል።

ይህንን ሀገርን የማጥፋትና የመበታተን እኩይ የወያኔና የውጭ ኃይሎች ተግባር ከጅምሩ ጀምሮ የተረዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወያኔን እየተፋለመ፡ እየታገለ፡ እየተዋደቀ ይገኛል። የትግሉም ጥንካሬና የሕዝቡም ልቆ አሳቢነት ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣት፡ ለወያኔ ሳይንበረከክ ሀገሬን፡ መብቴን፡ ብሎ ከዳር እስከ ዳር በዘር፡ በሃይማኖት፡ በፆታ፡ በዕድሜ፡

በክልል ሳይለያይ አንድ ሆኖ ወራሪውን ወንበዴ ቡድን እየታገለና እየተዋደቀ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የትግሉ ሚና ለይቷል። በአንድ በኩል በሕዝብ የሚመራው ኢትዮጵያን የማዳን ኃይልና በሌላ በኩል በውጭ ኃይሎች የሚመራው ወራሪው አገዛዝ፣ ወያኔ ተፋጠው ይገኛሉ። ሕዝብ ሀገሩን ሊያድን፣ ወያኔ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ሊያጠፋ የተጀመረው ትግል ቀጥሏል። ፍልሚያው በሁሉም አቅጣጫ ጋብ አላለም። በዚህም አካሄድ አንድ ሆኖ ለተነሳ ሕዝብ የሚያግደው አንዳችም ወያኔ ሰራሽ አይደለም ዓለም ሰራሽ ኃይል አይኖርም። አሁንም ሀገር በቀል ከሀዲዎችና ባንዳዎች ትግሉን አቅጣጫ ለማሳት ቢያቆጠቁጡም፣ የመጨረሻው የድል ባለቤት በሕዝቡ የሚመራው ኢትዮጵያን የማዳን ኃይል እንደሚሆን ጥርጥር ሊገባን አይገባም።

ይህ ለሀገር ህልውና የሚደረገው ፍልሚያ አሁንም ይበልጥ መቀነባበርን፣ በድርጅታዊ አሰራር መመራትን፣ መደራጀትን ይጠይቃል። ሕዝቡ በአመቸው የትግል ስልት በመጠቀም ፀረ - ወያኔ ተጋድሎውን እያፋፋመ ይገኛል። ወያኔ ወዳጅ እናደርገዋለን ብለው የተነሱበትንም ዳግማዊ ከሀዲና ባንዳዎች “ከእባብ እንቁላል እርግብ” እየተረተባቸው ይገኛል። በሌላም በኩል በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ እየተንቀሳቀሱ ላሉ የአንድነት ኃይሎችና የፖለቲካ ድርጅቶች አሁንም ተባበሩ፣ ትግሉንም መርቶ ከግብ ለማድረስ፣ በወያኔ ጠላትነት ላይ ብዥታ ሳይኖራችሁ፣ ቁርጠኝነቱ ይኑራችሁ ይላል። ሀገሪቷን ከውድመት በማዳን ጉዳይ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ በአንድነት ይተባበር ይላል ዛሬም እንደትላንቱ። መቃብሩ አፋፍ ላይ ቆሞ እየተወራጨ ያለውን ወያኔ፣ የሞት ጣር ላይ ያለውን ወያኔ፣ በውጭ ኃይሎች ጉሉኮስ እየተነፈሰ ያለውን ወያኔ፣ የመጨረሻ ሞቱን ለማብሰር ሁሉም በአንድነት፣ በቆራጥነት፣ ለነፃነትና ለሀገራችን ክብር መስዋዕትነት ይከፈል ይላል የሕዝብ ድምጽ።

ሕዝቡ ከሀገር ጠላት ጋር ለተባበሩትም ሆነ እየተባበሩ ላሉት ጊዜው ሳይመሽ ወደ ሕዝብ ጎራ እንዲቀላቀሉ ጥሪውን እያቀረበ፣ ለወያኔና ከሀዲ ባንዳዎች ትምህርት የሚሰጥበት ወቅት ሩቅ አይሆንም። በዚህ ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ላይ በግለሰብም ሆነ በድርጅት የተከሰቱ ከሀዲዎችና ያደቡ ጠላቶች አይተናል። እያየንም ነው። ሕዝብ የጣለባቸውን ሀላፊነት ወደ ጎን በማድረግ፣ በሀገሪቷ ቀጣይ ዕድል ላይ በዱለታ ላይ ያሉ ኃይሎች፣ ወደ ጥፋት ማጥ በመግባት ለተቅበዘበዙትና ለሚቅበዘበዙት ሕዝብና ታሪክ እንደሚፋረዳቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ግድ ይላል።

ትግላችን መራራ፣ መስዋዕትነት የሚጠይቅ መሆኑን ከተገነዘብን 16 ዓመታት ቢያልፈንም፣ አሁንም ጽናታችንን ጠብቀን ከሕዝብና ከሀገር ጐን ተሰልፈን በወያኔ መቃብር ላይ ኢትዮጵያ ታብብ ዘንድ በጋራ እንነሳ። የውጭ ኃይሎች ለወያኔ የሚያደርጉትን ድጋፍ እንዲያቆሙ በተደጋጋሚ አሳስበናል። ጠይቀናል። ወያኔን ለመጣል ግን ማንንም አለመንም። አንለምንምም። ለማንም ጭራ አንቆላም። ከእኛው ከራሳችን በላይ፣ ከተባበረ ሕዝብ በላይ የለምና ወያኔን እየተፋለምን በየጊዜው፣ አሁንም፣ ወደፊትም ሊገጥሙ በሚችሉ ከሀዲ ግለሰቦች፣ የድርጅት መሪዎችና ወይም ድርጅት ከቶም ልንደናገጥና ተስፋ ልንቆርጥ አይገባም። ይልቁንም ትግሉ አቅጣጫውን እንዳይስት፣ ዒላማውን እንዳያጣ ነቅተን መጠበቅ ይኖርብናል። ሕዝብን እንደ ወንዝ መሻገሪያ ታንኳ ሊጠቀሙበት ከሚያስቡ ኃይሎች እራሳችንን ልንጠብቅ ይገባናል፣፤ ትግላችን የሀገርና የሕዝብ ሕልውና ጉዳይ ነው ስንል፣ ማንኛውንም በመካከላችን ያሉትን መለስተኛ ቅራኔዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ አድርገን በአንድ ድምጽና ኃይል አገራችንን ነፃ እናውጣ ማለታችን ነው። በመተባበርና በጋራ የምናደርገው የተቀናጀ ትግል የድሉንም ጊዜ ከማቅረቡ ባሻገር ሊከፈል የሚያስገድደውን መስዋዕትነት እንደሚቀንስ መገመት ይኖርብናል።

የመለስ አገዛዝ መንገዳገድ ያስደነገጣቸው ባዕዳን ኃይሎች፣ እየቦጠቦጧት ያለችው ኢትዮጵያ እንዳታመልጣቸው የሰጉት፣ ከጥቅማቸውና ከፍላጎታቸው አንፃር ሌላ ተረኛ ሀገር አጥፊ፣ ሌላ

አምባገነን፡ ሌላ አፋኝ፡ የሀገርና የሕዝብ ጭምብል ያጠለቀ ከሀዲና ባንዳ እያዘጋጁልን ነው። አቀጣጫቸው ጥፋት፡ ሂደታቸው ሀገር መሸጥ፡ ግባቸው ሕዝብን ማፈን፡ ነውና አሁንም ከቀደምት ከሃዲዎች ትምህርት በመቅሰም ልንጠነቀቅ ይገባናል።

ወያኔም ባቅሙ ንቋቸው እንቀፍህ ቢሉት ጀርባውን እየሰጣቸው፡ እንጨብጥህ ቢሉት እየሸወዳቸው፡ እንወያይ ቢሉት እያላገጠባቸው፡ እሺ አንተ ባልከው ቢሉት ልጋልባችሁ እያላቸው፡ እሺ ጋልበን ቢሉት ትንሽ ቆዩ ሲላቸው፡ ቅሌት ቀለባቸው፡ ፍርሃት ልባቸው፡ ውርደት ጓደኛቸው ከሆኑ ዳግም በቀል ከሀዲና ባንዳዎች እንጠንቀቅ።

በዚህ የወያኔ መጨረሻ ምዕራፍ ላይ፡ በዚህ የሞት የሽረት የትግል ወቅት፡ በዚህ ሕዝብ የድል ደረጃውን እየወጣ፡ ጠላት የሞት ደረጃውን እየወረደ በአለበት ሂደት ዳግም በቀል ባንዳዎች፡ ከሀዲዎች ሲፈጠሩ ማየቱ አሁንም የጠላቶቻችን ሴራ ምን ያህል የተቀነባበረ መሆኑን በመረዳት ተስፋ መቁረጥን ሳይሆን ጥንካሬን ማዳበር ይገባናል።

ጉልበቴ በርታ በርታ ትሆነኛለህ መከታ፡
አጠማሃለሁ የድሉን ጽዋ፡ አሁንም አይደል ወደ ማታ።

ብለን ከሀገርና ሕዝብ ጐን ተሰልፈን የትግሉ አጋር መሆን የሚጠበቅብን ወሳኝ ጊዜ ላይ ደርሰናል።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወንበዴው ወያኔ ላይ ድልን በመቀዳጀት ጆሮአችን አይሰማም፡ ዓይናችን አያይም፡ አፋችን አይናገርም ብለው ያፌዙብንን የውጭ ኃይሎች እንዳላችሁት ያድርግላችሁ ብለን የምናሳፍርበት ወቅት ሩቅ አይሆንም።

ድል እርቆባቸው የወያኔን ወንበር ናፋቂ ከሀዲና ባንዳ የድል እንቅፋቶችን የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ መቃብር ላይ ሆኖ ታሪክ ይፋረዳቸው ዘንድ መጠየቁ አይቀሬ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!